# 2026 የነዋሪዎች የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ የመረጃ ብሮሹር



*የ2026 ዓ.ም የፈቃድ ፎቶ በIsabella Cappabianca*

CITY OF CAMBRIDGE | Department of Transportation

**የአማርኛ፣ አረብኛ፣ ባንግላ፣ የተቃለለ ቻይንኛ፣ የሄይቲ ክሪዮል፣ ፖርቱጋልኛ እና የስፓኒሽ ቋንቋ ትርጉሞችን ለማግኘት ኪው.አር ኮዱን (QR code) ስካን ያድርጉ።**

ትርጉሙን ለማንበብ ኮዱን ይቃኙ።

امسح الكود لقراءة الترجمة.

অনুবাদ পড়তে কোড স্ক্যান করুন।

扫码阅读翻译。

Eskane kòd pou li tradiksyon an.

Escaneie o código para ler a tradução.

Escanee el código para leer la traducción.


**Yi-An Huang, City Manager**
**ኮሚሽነር Brooke McKenna**
344 Broadway፣ Cambridge፣ MA 02139
cambridgema.gov/rpp | 617-349-4700

# የነዋሪ እና የጎብኚ ፈቃድ ደንቦች

**cambridgema.gov/parkingpermits ድኅረ-ገጽ ላይ የበለጠ ይወቁ።**

እነዚህን ደንቦች መተላለፍ እስከ $300 ሊደርስ የሚችል በእያንዳንዱ ጥፋት ላይ የሚጣል ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።

## የነዋሪዎች መኪና ማቆሚያ ፈቃዶች

- ፈቃዶቹ በተሽከርካሪው የፊት መስታወቱ የታችኛው የአሽከርካሪ ጎን ጥግ ላይ በውስጥ በኩል ተጣብቀው መቆየት አለባቸው።
- ፈቃዱ ላይ ያለው ቁጥር እና የተሽከርካሪው የታርጋ ቁጥር አንድ ዓይነት መሆን አለባቸው።
- አዲስ መኪና መያዝ ከጀመሩ ወይም የታርጋ ቁጥርዎ ከተለወጠ ከዚህ ቀደም ሲጠቀሙበት የነበረውን ፈቃድ እየተጠቀሙ መቀጠል አይችሉም።
- ፈቃዱን ኮፒ ማድረግ ወይም ለሌላ ተሽከርካሪ ማስተላለፍ የለብዎትም።
- የፈቃዱን ይዘት ከቀየሩ ወይም ደግሞ የተለጠፈበትን ቦታ ከለወጡ ፈቃዱ የሚሰረዝ ሲሆን፣ ፈቃዱን ሲያሳይ የተገኘ ተሽከርካሪም ቅጣት ይጣልበታል።
- ከ Cambridge ከተማ ወጥተው ሌላ ቦታ መኖር ከጀመሩ ፈቃድዎን ያስወግዱ።
- ሁሉም ፈቃዶች ማርች 31 ቀን 2027 ዓ.ም ላይ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃል።

## የጎብኚዎች መኪና ማቆሚያ ፈቃዶች

የጎብኚዎች የመኪና ማቆሚያ ፈቃዶች ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች የነዋሪውን ቤት ሲጎበኙ «Parking by Permit Only (በፈቃድ ብቻ መኪና ማቆም የሚቻልባቸው)» አካባቢዎች ላይ እንዲያቆሙ ያስችላቸዋል። ጎብኚዎቹ ከእያንዳንዱ ጉብኝት በኋላ ፈቃዱን ለነዋሪው መመለስ ይኖርባቸዋል።

## የጎብኚዎች መኪና ማቆሚያ ፈቃዶችን መጠቀም የሚችለው ማን ነው?

- የጎብኚ ፈቃዶቹን መጠቀም የሚችሉት የCambridge ነዋሪዎች እንግዳዎች ብቻ ናቸው።
- ፈቃዶቹ የሚያገለግሉት ለጉብኚው በተሰጠው የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ የጀርባ ገጽ ላይ ለተቀመጠው ቦታ ብቻ ነው።
- ታክሲዎች፣ በቅጥር የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች እና በመጠናቸው ግዙፍ የሆኑ ተሽከርካሪዎች የጎብኚ ፈቃዶችን መጠቀም አይችሉም።

## ደንቦቹ ምን ምን ናቸው?

- የጎብኚ ፈቃዶችን ኮፒ ማድረግ፣ መሸጥ፣ ማስተላለፍ ወይም ፈቃዱ ውስጥ የሰፈሩትን ነገሮች መቀየር የለብዎትም።
- ተሽከርካሪዎቹ ከ24 ሰዓታት በኋላ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።
- ተሽከርካሪዎች በሳምንት ከሶስት ቀናት በላይ በተመሳሳይ ቦታ ማቆም አይችሉም (እሁድን ሳይጨምር)።
- የከተማው አስተዳደር በጎብኚዎች ፈቃድ አጠቃቀም ላይ ክትትል ያደርጋል። አንድ የጎብኚ ፈቃድ በአንድ ተሽከርካሪ ላይ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ከዋለ በተሽከርካሪው ላይ ቅጣት ልንጥል እና/ወይም ፈቃዱን ልንሽር እንችላለን።
- Cambridge ውስጥ ከገቡ Parking Services (የመኪና ማቆሚያ አገልግሎቶችን) ያነጋግሩ። ፈቃድዎን መቀየር ሊያስፈልግዎ ይችላል።




# የፈቃድ አቀማመጥ

## ፈቃዶቹ እዚህ መሆን አለባቸው።

ባለፉት ዓመታት የተሰጡ ፈቃዶችን በሙሉ ያስወግዱ።

ፈቃዶቹ በተሽከርካሪው የፊት መስታወቱ የታችኛው የአሽከርካሪ ጎን ጥግ ላይ በውስጥ በኩል ተጣብቀው መቆየት አለባቸው።

የጎብኚ መኪና ማቆሚያ ፈቃዶች መቀመጥ ያለባቸው በጎብኚው መኪና ዳሽቦርድ ላይ ነው።

መኪናዎን ሁሉንም የከተማውን የትራፊክ ምልክቶች እና ደንቦች በመከተል እና በማክበር ያቁሙ።

# የመንገድ ጽዳት ማሳሰቢያ

የከተማው አስተዳደር በCharles River እና Alewife Brook ጎዳናዎች ላይ የውኃ ጥራትን ለማሻሻል እና ለመጠበቅ መንገዶቹን የሚጠርጋቸው ይሆናል።

የከተማው አስተዳደር ለመንገድ ጽዳት አስቸጋሪ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን እንዲነሱ የማያደርግ ሲሆን፣ ይልቁንም ግን ያልተንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የ$100 ዶላር ቅጣት የሚጣልባቸው ይሆናል።

የጊዜ ሰሌዳውን ተመልክተው፣ የቅጣት ትኬት እንዳይጣልብዎ እና መንገዶቻችንን ንጹሕ ለማድረግ መኪናዎን ያንቀሳቅሱ!

# የCambridge የመኪና ማቆሚያ እና የመንገድ ማስታወሻዎች

## የመኪና ማቆሚያ መለኪያ ደንቦች

- በሃያ አምስት ሳንቲሞች (ኳርተርስ) ወይም በመኪና ማቆሚያ የሞባይል መተግበሪያው ተጠቅመው ይክፈሉ።
- ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ አያቁሙ።
- እሁድ እና በMA በዓላት ቀን የመኪና ማቆሚያው ነጻ ነው።
- የአካል ጉዳተኞች ፈቃድ/የሰሌዳ ቁጥር የያዙ ተሽከርካሪዎች ያለምንም የጊዜ ገደብ በነጻ ማቆም ይችላሉ።


## የተሰበረ የክፍያ ጣቢያ ወይስ ቆጣሪ አጋጥሞዎትል?

የክፍያ ጣቢያ ወይም ቆጣሪ ተሰብሯል ወይም አይሠራም ብለው ካሰቡ በመኪና ማቆሚያ የሞባይል መተግበሪያው በኩል መክፈል ወይም በሌላ ቦታ ማቆም ይኖርብዎታል።

የተበላሸ የመኪና ማቆሚያ ክፍያ መፈጸሚያ ማሽንን ሪፖርት ለማድረግ በ 617-349-4700 ይደውሉ።

# የዲስትሪክቶች የመንገድ ጽዳት ካርታ

የመንገድ ጽዳት ማሳሰቢያዎቹ እንዲደርሱዎ **ወደ cambridgema.gov/StreetCleaningReminders በመሄድ ይመዝገቡ።**




**የሚከተሉትን ያካትታል፦** Griswold St፣ Normandy Ave፣ Normandy Ter፣ South Normandy Ave እና Sunset Rd።

የDistrict C አካል

**የሚከተሉትን ያካትታል፦** Education Cir፣ Education St፣ Museum Way እና North Point Blvd።

# የ 2026 ዓ.ም የመንገድ ጽዳት መርሃ-ግብር

*ምልክቱ በበዓል ምክንያት የተደረገ የጽዳት መርሃ-ግብር ለውጥን ያመላክታል
617-349-4800 | cambridgema.gov/theworks

| ዲስትሪክት | የመንገድ ጎን ቁጥር | ቀን | ኤፕሪል | ሜይ | ጁን | ጁላይ | ኦገስት | ሴፕቴምበር | ኦክቶበር | ኖቬምበር | ዲሴምበር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| A | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 1ኛው ረቡዕ | 1 | 6 | 3 | 1 | 5 | 2 | 7 | 4 | 2 |
| A | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 1ኛው ሐሙስ | 2 | 7 | 4 | 2 | 6 | 3 | 1 | 5 | 3 |
| B | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 1ኛው ሰኞ | 6 | 4 | 1 | 6 | 3 | ኦገስት-31* | 5 | 2 | 7 |
| B | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 1ኛው ማክሰኞ | 7 | 5 | 2 | 7 | 4 | 8 | 6 | 3 | 1 |
| C | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 1ኛው አርብ | 3 | 1 | 5 | ጁን-30* | 7 | 4 | 2 | 6 | 4 |
| C | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 2ተኛው ሰኞ | 13 | 11 | 8 | 13 | 10 | 14 | ሴፕቴምበር-29* | 9 | 14 |
| D | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 2ተኛው ማክሰኞ | 14 | 12 | 9 | 14 | 11 | 8 | 13 | 10 | 8 |
| D | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 2ተኛው ረቡዕ | 8 | 13 | 10 | 8 | 12 | 9 | 14 | ኦክቶበር-29* | 9 |
| E | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 2ተኛው ሐሙስ | 9 | 14 | 11 | 9 | 13 | 10 | 8 | 12 | 10 |
| E | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 2ተኛው አርብ | 10 | 8 | 12 | 10 | 14 | 11 | 9 | 13 | 11 |
| F | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 3ተኛው ሰኞ | ኤፕሪል-29* | 18 | 15 | 20 | 17 | 21 | 19 | 16 | 21 |
| F | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 3ተኛው ማክሰኞ | 21 | 19 | 16 | 21 | 18 | 15 | 20 | 17 | 15 |
| G | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 3ተኛው ረቡዕ | 15 | 20 | 17 | 15 | 19 | 16 | 21 | 18 | 16 |
| G | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 3ተኛው ሐሙስ | 16 | 21 | 18 | 16 | 20 | 17 | 15 | 19 | 17 |
| H | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 3ተኛው አርብ | 17 | 15 | ጁን-29* | 17 | 21 | 18 | 16 | 20 | 18 |
| H | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 4ተኛው ሰኞ | 27 | ሜይ-29* | 22 | 27 | 24 | 28 | 26 | 23 | 28 |
| J | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 4ተኛው ማክሰኞ | 28 | 26 | 23 | 28 | 25 | 22 | 27 | 24 | 22 |
| J | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 4ተኛው ረቡዕ | 22 | 27 | 24 | 22 | 26 | 23 | 28 | 25 | 23 |
| K | ጎዶሎ ቁጥር | የወሩ 4ተኛው ሐሙስ | 23 | 28 | 25 | 23 | 27 | 24 | 22 | ኖቬምበር-30* | 24 |
| K | ሙሉ ቁጥር | የወሩ 4ተኛው አርብ | 24 | 22 | 26 | 24 | 28 | 25 | 23 | 27 | 29-ዲሴምበር* |

## የመገኛ አድራሻ

**የCambridge ከተማ አስተዳደር**
617-349-4000 | cambridgema.gov

**Department of Transportation (የትራንስፖርት መምሪያ)**
617-349-4700 | cambridgema.gov/Transportation

**ለፖሊስ አገልግሎት (ድንገተኛ ላልሆኑ ክስተቶች) እና ተጎትተው የተነሱ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ**
617-349-3300 | cambridgema.gov/TowedVehicles

የተጠቀሱት ስልክ ቁጥሮች በሙሉ የድምጽ ጥሪ መስመሮች ናቸው። በ711 (ሪሌይ) ላይ በመደወልም ሊያገኙን ይችላሉ።

## ይህንን ብሮሹር በኦንላይን ያንብቡ

www.cambridgema.gov/2026rpp

## የተደራሽነት መረጃ

የ Cambridge ከተማ አስተዳደር አካል ጉዳተኝነትን መሠረት ያደረገ መድልዎን ጨምሮ በሌሎች ማናቸውም ዓይነት መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ መድልዎን አይፈጽምም። አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች ቁሳቁሶች በተለያዩ ቅርፀቶች እንዲቀርቡ እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ ማሻሻያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ እንችላለን።

## እገዛ ይፈልጋሉ?

ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም እርዳታ ካስፈለግዎት በtpt@cambridgema.gov፣ 617-349-4700 ወይም 711 (ሪሌይ) በኩል ያግኙን።

## የ2027 ዓ.ም የእድሳት ጊዜ

*በሚቀጥለው ዓመት እንገናኝ!*

**የ2026 ዓ.ም ፈቃድዎ የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃው ማርች 31 ቀን 2027 ዓ.ም ላይ ይሆናል።**

የ2027 ዓ.ም የነዋሪዎች/የጎብኚዎች ፈቃድ ወቅት የሚጀምረው ጃንዋሪ 2 ቀን 2027 ዓ.ም ላይ ይሆናል። የ2026 ዓ.ም ፈቃድዎን በኦንላይን ወደ **cambridgema.gov/parkingpermits** በመሄድ ከዲሴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም ጀምሮ ማደስ ይችላሉ።